የሰ/መ/ቁ. 46143

ሐምሌ 2 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ድልበጌ ራሕመቶ

**ተጠሪዎች፡-** 1. የባህር ትራንዚት አገልግሎት ድርጅት - ነ/ፈጅ መላኩ መኰንን

2. የአቶ መሐመድ ዑስማን ወራሾች - ሙሠማ መሐመድ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአፈጻጸም ጊዜ የተነሳን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው አንደኛ አመልካች የፍርድ ባለመብት ሲሆን የሁለተኛ ተጠሪዎች አውራሽ አቶ መሐመድ ዑስማን ደግሞ የፍርድ ባለዕዳ ነው፡፡ አመልካች ክርክሩ ውስጥ የገባችው የፍርድ ባለመብቱ የአፈጻጸም ትዕዛዝ (በሐራጅ ይሸጥ) ያሰጠበት ቤት የፍርድ ባለዕዳ ንብረት አይደለም፡፡ ቀደም ሲል ኑርሑሴን በርሄ የተባለው ሰው ንብረት የነበረ፤ በኋላም ከዚህ ሰው ወራሾች (እነ ዘይኑ ኑርሑሴን) ላይ የገዛሁት ነው፡፡ በንብረቱ ላይ የተሰጠው የሐራጅ ትዕዛዝ እና እግድ ይነሳልኝ በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.418 መሠረት በማለት መቃወሚያ በማቅረብዋ ነው፡፡ መቃወሚያው የቀረበለት ፍ/ቤት የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ የአመልካችን መቃወሚያ በመቀበል የሐራጁ ሽያጭ ቀሪ ሆኖ ቤቱ ለአመልካች ይለቀቅ በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንደኛ ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም አመልካች ቤቱን ገዝቻለሁ በማለት ውል ከማቅረብዋ ውጪ ስመሃብቱን በስምዋ አላዛወረችም፡፡ ባለቤት ናት ለማለት የሚያስችል ማስረጃ የላትም የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት መቃወሚያው ተቀባይነት የለውም ብሎአል፡፡ በዚህ መሠረትም በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት የአመልካችን ይግባኝ ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 24 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት በውል መገዛት እየታወቀ በስምሽ አልተመዘገበም በሚል ምክንያት መቃወሚያዬ ውድቅ መደረጉ አግባብ አይደለም የሚለውን የአመልካች አቤቱታ ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

ክርክሩ በአፈጻጸም ደረጃ ያለን ጉዳይ የሚመለከት ስለመሆኑ ከላይ ተገልጾአል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ቤቱን በአፈጻጸም እንዲያዝለት የጠየቀው የፍርድ ባለዕዳው የአቶ መሐመድ ዑስማን (የሁለተኛ ተጠሪዎች አውራሽ) ንብረት ነው በማለት ነው፡፡ አመልካች ቤቱን ገዛሁት የምትለው ደግሞ ከፍርድ ባለዕዳው ላይ ሳይሆን፣ አቶ ኑርሁሴን በርሄ ከተባለው ሰው ወራሾች ላይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ያቀረበችው መቃወሚያ አንደኛ ተጠሪ ከአቀረበው ክርክር አንፃር ከመታየቱ በፊት በእርግጥ ቤቱ የፍርድ ባለዕዳው ንብረት ለመሆኑስ ተረጋግጦአል ወይ? የሚለውን ነጥብ መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ አንደኛ ተጠሪ በዚህ ረገድ አንድም ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ ሲከራከር የቆየው አመልካች የሽያጭ ውል ከማቅረብ አልፋ የቤቱን ስመሃብት በስምዋ አላዛወረችም በሚለው ነጥብ ላይ ብቻ በመመስረት ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ይህን የክርክር አቅጣጫ ተከትለው ነው የወሰኑት፡፡ በበኩላችን እንደምናየው ግን ለሽያጭ የቀረበው /አንደኛ ተጠሪ በአፈጻጸም ያስያዘው/ ቤት በእርግጥም የፍርድ ባለዕዳው ንብረት ለመሆኑ በቅድሚያ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ይህ ከተረጋገጠ በኋላም ነው በአመልካች እና በአንደኛ ተጠሪ መካከል ያለውን ክርክር ማየት የሚገባው፡፡

ከላይ እንዳመለከትነው አመልካች ቤቱን የገዛችው ከፍርድ ባለ ዕዳ ላይ እንዳልሆነ አላከራከረም፡፡ አንደኛ ተጠሪም ቤቱ የፍርድ ባለዕዳ ንብረት ለመሆኑ ወይም የአቶ ኑርሁሴን በርሄ ንብረት ላለመሆኑ በማስረጃ ሊያስረዳ ቀርቶ በክርክር ደረጃ እንኳን ምንም ያለው ነገር የለም፡፡ በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክርም የአንደኛ ተጠሪ ነገረ-ፈጅ ተጠይቆ የሰጠው መልስም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ በሁለተኛ ተጠሪነት የቀረቡት የሥር የፍርድ ባለዕዳ ወራሾችም ቤቱ የእነሱ እንዳልሆነ በመግለጽ መልስ ሰጥተዋል፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ስናየው ቤቱ አንደኛ ተጠሪ በሁለ ተኛ ተጠሪ ባስፈረደው ገንዘብ ምክንያት በአፈጻጸም የሚያዝበት የሕግ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ስለዚህም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## **ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 68424 የካቲት 5 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 44935 ሚያዝያ 19 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ለክርክሩ መነሻ የሆነው በአፈጻጸም ሊያዝ አይችልም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

# ወንጀል